# የተፈታህ ቋጥር!

(አንሙት ከለንደን፣ መስከረም 1998)

የተፈታህ ቋጥር!
የላላብህ ወጥር!
የዋለልክም ጠጥር!
የለሰለስክ አምርር!
ቀበቶህን አክርር!
አቋምህን አፅና፣ ትግልህን አጠንክር!
እርስ በርስህ አብር!
የህዝብን ይሁንታ፣ ድምፅ ልታስከብር!

መንገድ ስትሰንቁ
ልትመራው! ሊመራህ!
ስትነቃነቁ!
ገና ከጠዋቱ
ከመነሻ ጉዞህ፣
የታሪካችሁ ዝክር
የማተብ ቀለምህ፣
የመሃላ ንባብ
የቃል ኪዳን ውልህ፣
ህዝብ እምነቱን ሰጥቶህ!
አንተም ለእሱ ሰጥተህ!
እየታገላችሁ!
እየወደቃችሁ!
ቢያሻ ተሰውቶ!
ቢያሻም ተሰውተህ!
ግንባር ቀደም ሆነህ!
ለድል ልታበቃው እንጅ ዳር አድርሰህ!
አይደለም ለወንበር
ፍርፋሪ ይዘህ፣
የሚፈሰውን ደም
ደመ-ከልብ አድርገህ!
በቀጣፊ ምላስ
ትእዛዝ ተሸቀጥቁጠህ!
የብዙኃኑን ድምጽ
ለዳረጎት ሰጥተህ!
የህዝብን ይሁንታ
በሾርኒ አስነጥቀህ!
ከዙፋን በማድረስ
ገዳዩን ሸልመህ!
መለስን ለማንገስ
በስርቆት አጅበህ!

አስታውስ! አትርሳ!
ፊትን ቃል በስራ!
የለኮሱት ችቦ
በድል ካላበራ!
የህሊና ጩኸት
የሙታኑ አደራ!
የሰማዕቱ ጥሪ
መቼም አያባራ!

የተፈታህ ቋጥር!
የላላብህ ወጥር!
የዋለልክም ጠጥር!
የለሰለስክ አምርር!
ቀበቶህን አክርር!
አቋምህን አፅና፣ ትግልህን አጠንክር!
እርስ በርስህ አብር!
የህዝብን ይሁንታ፣ ድምፅ ልታስከብር!

በድምፅ አይሰረቅ!
በእምቢ! በመጽናቱ!
በጥይት ተመትቶ
ፈርሶ ጭንቅላቱ!
ህይወቱን የሰዋው
ወጣቷ፣ ወጣቱ!
ለእምነት ተሰይፎ
ይዞሃል በእምነቱ!
ከመለስ ጉረኖ
በረት ከመግባቱ!
በደሙ ተገዝት
ተከልክል ባጥንቱ!
ቆምጨጭ በል! ተፀፅት
ይቆጭህ መሞቱ!
ለአላማው መሳካት
ህይወቱን መስጠቱ!
ታመነው ላደራው
ለቆራጥነቱ!
ገድሉን ተረከበው
ክቡር ቤዛነቱ!
ፋና ወጊህ ይሁን!
ሰማዕት፣ ሰማዕቲቱ!
ሞት አያሸብርህ!
ሞት ሞቷል ሲሞቱ!
አርማቸውን አንሳ
አሁን ነው ሰአቱ!

የተፈታህ ቋጥር!
የላላብህ ወጥር!
የዋለልክም ጠጥር!
የለሰለስክ አምርር!
ቀበቶህን አክርር!
አቋምህን አፅና፣ ትግልህን አጠንክር!
እርስ በርስህ አብር!
የህዝብን ይሁንታ፣ ድምፅ ልታስከብር!